# በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስትየቱሪዝም ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም እንደገና ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 106/2005

## መግቢያ

ክልሉ የተለያዩ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መኖሪያና የተፈጥሮአዊ ሀብቶች መገኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የብዙ ባህላዊ፣ታሪካዊና ተፈጥሮአዊ የቱሪስት መስህቦችና መዳረሻዎች ባለቤት በመሆኑ፣

በክልሉ በስፋት የሚገኙ የቱሪስት መስህቦች ለክልሉ ብሎም ለሀገሪቱ ዘላቂ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎችን ለማስገኘት ለድህነት ቅነሳው ተገቢውን ድርሻ ማበርከት እንዲችሉና የአካባቢው ህብረተሰብን ቀጥተኛ ተጠቃሚነት ማሳደግ በማስፈለጉ፣

በቱሪስት መስህቦች አካባቢ ቀጣይነት ያለውየመሰረተ ልማት አውታሮችን በመገንባትና በማስፋፋት የመስህቦቹ የአገልግሎት ክፍያ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ካለው የቱሪስት እንቅስቃሴና ከሀገሪቱ የውጪ ምንዛሪ ዋጋ ጋር አጣጥሞ ገቢውን በማሳደግ መስህቦቹ ቀስ በቀስ ራሳቸውን ማስተዳደር እንዲችሉ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት በክልሉ የአስፈጻሚ አካላት ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 133/2003 አንቀጽ 45/3ሀ መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ <<የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥትየቱሪዝም ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ደንብ ቁጥር 106/2005>> ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ት ር ጓ ሜ**

የቃሉ ትርጓሜ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1. #ሰው; ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
2. #ክልል;ማለት የደቡብ ብሄሮች፣ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ነው፤
3. #**ቢሮ**; ማለት የክልሉ መንግስት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ነው ፡፡
4. #**መምሪያ**; ማለት የዞን ባህል፣ ቱሪዝምና መንግሥት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ ነው፤
5. #**ጽ/ቤት**; ማለት የልዩ ወረዳና የወረዳ ባህል፣ ቱሪዝምና መንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ነው፤
6. #**ብሔራዊ ፓርክ**; ማለት ለዱር ሕይወት፣ ለሥነ ምህዳር ጥበቃ፣ ለመዝናኛነት፣ ለሣይንሣዊ ጥናትና ምርምር የሚያግዙ ቦታዎችን ለመጠበቅና ለመንከባከብ የተከለለ መሬት ወይም በውሃ የተሸፈነ ምንም ዓይነት የአደን፣የእርሻ፣ከብቶችንየማስጋጥ፣ዛፎችንየመቁረጥ፣ዕፅዋትንየማቃጠል፣ጎጆዎችንቀልሶለመኖርየተከለ ከለበት በክልሉ መንግስት ባለቤትነት የተያዘ ሥፍራነው፡፡
7. #**ቁጥጥር አደን ቀበሌ** ;ማለት የዱር ሕይወታዊ ሀብት ጥበቃ የሚካሄድበት ቦታ ሆኖ ነገር ግን በክልሉ መንግስት የሚተዳደር ወይም በኪራይ ለአሳዳኝ ድርጅት የሚሰጥ በሳይንሳዊ መንገድ የዱር እንስሳት ሰፖርታዊ አደን የሚካሄድበት ቦታ ነው፡፡
8. #**በህብረተሰብ የሚተዳደሩ የቱሪስትመስህቦች**;ማለት በቢሮው ወይም በተዋረድ በሚገኙ እርከኖችአደራጅነት የሚቋቋም እና በእነዚሁ አካላት ድጋፍ በዋነኝነት ከህብረተሰቡ በተወከሉ አመራሮች የሚተዳደር ተፈጥራዊ፣ ባህላዊ ወይም ታሪካዊ የቱሪስት መስህብ ማለት ነው፡፡
9. #**የዱር እንስሳት የጥበቃ ክልሎች**; ማለት ለዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት ሥራ የተከለሉሥፍራዎችሲሆኑ ብሔራዊ ፓርክን፣ የቁጥጥር አደን ቀበሌን፣ ጥብቅ የዱር እንስሳት ክልልንእንዲሁም ለወደፊት በክልሉ መንግስት የዱር እንስሳት የጥበቃ ክልል ተብለው የሚከለሉትን ሥፍራዎች ጭምር ያካትታል፡፡
10. #**ፓርኪንግ**;ማለት በመስህቦች መዳረሻ ላይ ባለሞተር ወይም ሞተር አልባ ተሽከርካሪዎች እንዲሁም በእንስሳት ለሚጎተቱ ተሽከርካሪዎች ማቆሚያነት አገልግሎት ለመስጠት ተለይቶ የተዘጋጀ ቦታ ነው፡፡

11. #**ስካውት»** ማለት በብሔራዊ ፓርክ፣ በቁጥጥር አደን ቀበሌ፣ በጥብቅ የዱር እንስሳት ክልሎች እንዲሁም አዞ ራንች ውስጥ የዱር እንስሳቱንና የመኖሪያ አካባቢያቸውን ደህንነት ለመጠበቅ፣ የዱር እንስሳቱን ባህርይና እንቅስቃሴ በቅርብ ለመከታተል የተመደበ ሠራተኛ ነው፡፡

12. #**አከባቢ አስጎብኚ»** ማለት በቢሮው ወይም በተዋረድ ባሉ መዋቅሮች በመደራጀት እና ስልጠና በመውሰድ በተወሰነ ቦታ የማስጎብኘት ሥራ የሚያከናውኑ ማህበራት ወይም ሰዎች ናቸው፡፡

13. #**ስፖርታዊ ዓሣ ማስገር´** ማለት ለመዝናናት ወይም ለእርስ በእርስ ውድድር በመንጠቆ የሚደረግ የዓሳ ማስገር ሥራ ሲሆን ዓሳውን ለምግብነት ለመጠቀም ወይም ወደ ተፈጥሮ መኖሪያው በመመለስ የሚከናወን ነው፡፡

14. #**የቱሪስት መስህብ**; ማለት የጎብኚን ትኩረት የሚስቡ ወይም የሚማርኩ ተፈጥሮአዊ፣ ባሕላዊና ታሪካዊ ቅርሶች ወይም ክንዋኔዎች ማለት ነው፡፡

15. #**ኢትዮጵያዊ**;ማለት በትውልዱ ወይንም በሕግ የኢትዮጵያዊነት ዜግነት የተሰጠውአካል ነው፡፡

16. #**የአደን ቦታ የመጠቀሚያ ግብር**;ማለት የቁጥጥር አደን ቀበሌን በዓመት ለተገደበ ጊዜ በኮንሴሽን ከክልሉ መንግስት ተረክቦ የተጠቀመ ያለ ድርጅት ወይም ሰው ለሚያገኘው ጥቅም ለቦታው በህግ ተወስኖ የሚከፍለው ዓመታዊ ክፍያነው፡፡

17. #**ገቢ**;ማለት ከጉብኝት ጋር በተገናኘ የሚሰበሰቡ የተለያዩ ክፍያዎች፣ ከአደን፣ ከአዞ ቆዳ ሽያጭ፣ ከአዞ ጫጩት ሽያጭ፣ ከትሮፊ ሽያጭ፣ ከአደን ቦታ መጠቀሚያ ግብር ወይም ከፊልም ቀረጻ የሚሰበሰብ ገንዘብ ነው፡፡

18. #**በትምህርት ቤቶች የተቋቋሙ ክበባት**;ማለት በሀገሪቱ ውስጥ ባሉት ት/ቤቶች አካባቢ ለማወቅ ለማድነቅና ለመጎብኘት በፈቃደኝነት የተቋቋሙ ክበባት ናቸው፡፡

19. #**የሀገርህን ዕወቅ ክበባት#** ማለት በሃገሪቱ ውስጥ ባሉ መንግስታዊ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ወይም የግል ድርጅቶች የሚሰሩ ሠራተኞች፣ሲቪክ ማህበራት ወይም ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች አካባቢን ለማወቅ፣ለማድነቅና ለመጎብኘት በፈቃደኝነት የመሰረቱት ክበባት ናቸው፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በክልሉ በሚገኙ በክልሉ መንግስት ባለቤትነት ስር በሚገኙ የቱሪስት መስህቦች ሁሉ ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

# ክፍ ል   ሁ ለ ት

## ገቢ የሚሰበሰብባቸው አገልግሎቶችና የክፍያ መጠን

## 4. ገቢ የሚሰበሰብባቸው  አገልግሎቶች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በቱሪስት መስህቦች ገቢ የሚሰበሰብባቸው አገልግሎቶች ናቸው፡፡

1. የመግቢያ
2. የአጃቢ እስካውቶች አገልግሎት
3. የአውሮፕላን ማረፊያና መቆሚያ አገልግሎት
4. በተሽከርካሪ የሚደረግ ጎብኝት ፣
5. በሞተር ብስክሌት የሚደረግ ጉዞ፣
6. በጀልባ የሚደረግ ጉብኝት ፣
7. የአስጎብኚ ድርጅቶች የማስጎብኘት አገልግሎት፣
8. የማረፊያ ሥፍራና ድንኳን አገልግሎት ፣
9. ለንግድ ሥራ የሚከናወኑ የፎቶ ግራፍና ፊልም ቀረጻ ሥራዎች፣
10. የአካባቢ አስጎብኚብዎች አገልግሎት፣
11. የስፖርት አደን ገቢ፣
12. የሀገር ውስጥ ነዋሪ አደን ፈቃድ መዋጮ፣
13. የዱር እንስሳት ጠመዳ ባለሙያ ፈቃድ ፣
14. የውጪ ተመራማሪዎች ሳይንሳዊ ጥናት ፣
15. የዱር እንስሳት ውጤቶች ንግድ ፈቃድ
16. የታክሲ ደርሚ ስራ ፈቃድ
17. የዱር እንስሳት እርባታ ፈቃድ
18. የአዞ፣ ጥርኝ፣ ሰጎን ነፍስ ወከፍ ዋጋ ተመን
19. ስፖርታዊ ዓሳ ማጥመድ

## 5. የአገልግሎት  የክፍያ መጠን

5.1 የአገልግሎት ክፍያ መጠን ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው አባሪ ሠንጠረዥ መሰረት ይሆናል፡፡

5.2 በየመስህቡ አካባቢ የሚደራጁ አስጎብኚ ማህበራት እንደሚሰጡት የአገልግሎት ዓይነት ክፍያቸው በመመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

5.3 የዱር እንስሳት አደን ዋጋ ተመን በፌደራል የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ደንብ ቁጥር 163 /2001 የተገለጸው ይሆናል፡፡

# ክፍል ሶስት

## በስምምነት ክፍያ የሚፈፀምባቸው እና ክፍያ የማይፈፀምባቸው አገልግሎቶች

### 6. በስምምነት ክፍያ የሚፈጸምባቸው አገልግሎቶች

1. የጋማ ከብቶቹ ኪራይ የሚከፈል ክፍያ በጋማ ከብት ባለቤት እና በጎብኚዎች መካከል በሚደረግ ስምምነት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

### 7. ክፍያ የማይፈጸምባቸው ሁኔታዎች

ከዚህ በታች የተመለከቱት ክፍያ የማይፈፀምባቸው ናቸው፤

1. ማንኛውም ዕድሜው ከ12 ዓመት በታች የሆነ ሕፃን ወይም ልጅ፤
2. ከየትኛውም አካባቢ ጎብኝዎችን ይዞ የሚመጣ ሾፌር
3. በዚህ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም በአንድ ተሽከርካሪ የሚሰሩት አሽከርካሪዎች ከአንድ በላይ ከሆኑ ለመክፈል የማይገደደው አንዱ አሽከርካሪ ብቻ ነው፡፡
4. ማንኛውም ቱሪስቶችን ይዞ የሚመጣ የጉብኝት መሪ ክፍያ አይፈጽምም
5. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀፅ 7.4 የተደነገገ ቢሆንም ለመጀመሪያ ጊዜ የሚመጣ የጉብኝት መሪ ወይም በአንድ የጉብኝት ቡድን ውስጥ ያለ ተጨማሪ የጉብኝት መሪ እንደ ማንኛውም ጎብኚ ክፍያ እንዲፈጽም ይደረጋል፡፡

## 8. የክፍያ ስርዓት

በውጭ ዜጎች የሚከፈል ክፍያ በሙሉ በአሜሪካን ዶላር ሆኖ በውጭ ገንዘብ ለመቀበል የሚያስችል አደረጃጀት በተፈጠረባቸውና ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ባገኙንባቸው ቦታዎች ክፍያ በቀጥታ በዶላር የሚፈጸም ይሆናል፡፡ ሆኖም ይህ ሁኔታ ባልተመቻቸባቸው ቦታዎች በእለቱ የውጭ ምንዛሪ ዋጋ መሰረት ክፍያው በብር የሚፈጸም ይሆናል፡፡

# ክ ፍ ል አራት

## ገቢ አሰባሰብ፣ ክፍፍልና አጠቃቀም

9. **የገቢ አሰባሰብ**

1. በክልል ከሚተዳደሩ ብሔራዊ ፓርኮች፣ አዞ ራንች፣ ቁጥጥር አደን ቀበሌዎች፣ ሌሎች መስህቦች ንዲሁም ለወደፊት በክልሉ ከሚከለሉ መስህቦች የሚሰበሰበው ገቢ በክልሉፋይናንስናኢኮኖሚልማትቢሮፈቃድለገቢ ማሰባሰቢያ በተቋቋመ የባንክ አካውንት እንዲገባ ይደረጋል፡፡

2. በክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በማይተዳደሩ የቱሪስት መስህቦች የሚኖረው የክፍያ አሰባሰብ መስህቦቹ በሚገኙበት ስፍራ የሚገኙ የዞን ፣ የልዩ የወረዳ ወይም የወረዳ ባህል ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ ወይም ጽ/ቤቶች በኩል ሆኖ በመንግስት ፋይናንስ ደንብ መሠረት መፈጸም ይኖርበታል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው ንደተጠበቀ ሆኖየተሰበሰበውገቢ ለዚሁ ዓላማ ተብሎ በተከፈተ የባንክሂሳብ እንዲገባ ይደረጋል፡፡

**10. ክፍፍልና አጠቃቀም**

10.1 ከብሔራዊ ፓርኮች፣ ቁጥጥር አደን ቀበሌዎች፣ አዞ ራንች፣ በሕብረተሰብ የሚተዳደሩ የጥበቃ ክልሎችና ሌሎች መስህቦች ንዲሁም ለወደፊት በክልሉ ከሚከለሉ የጥበቃ ክልሎችና መስህቦች ከሚገኝና ከሚሰበሰበው ገቢ የክፍፍል ሥርዓት በሚከተለው ሁኔታ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

1. ከብሄራዊ ፓርክ
   - ሀ. ለብሄራዊ ፖርኩ ልማት ____________________ 60%
   - ለ. ለአካባቢ ህብረተሰብ ____________________ 30%
   - ሐ. ለክልል ____________________ 10%
2. ከቁጥጥር አደን ቀበሌ
   - ሀ.. ለአካባቢው ሕብረተሰብ ____________________ 20%
   - ለ. ለጥበቃ ቦታዎች ልማት ____________________ 70%
   - ሐ. ለክልል ____________________ 10%

3. ከራንቾች

ሀ. ለራንቹ ልማት_________________________________________________70%

ለ. ለአካባቢው ሕብረተሰብ _________________________________________20%

ሐ. ለክልል_____________________________________________________10%

## 4. ህብረተሰቡ ከሚያስተዳድራቸው ጥበቃ ቦታዎች ወይም ሌሎች የቱሪስት መስህቦች

ሀ. ለመስህብ ቦታው ልማት _____________________________________40%

ለ. ለአካባቢ ህብረተሰብ_______________________________________40%

ሐ. ለመስህቡ መገኛ ወረዳ ____________________________________20%

10.2 በሁለት ዞኖች ወይም በአንድ ዞንና ልዩ ወረዳ ወይም በሁለት ወረዳዎች በአጠቃላይ ከሁለት በላይ በሆኑ የአስተዳደርአርከኖችመካከል የሚገኙ የዱር እንስሳት የጥበቃ ክልሎች ወይም መስህቦች የሚገኝየሕብረተሰብ ገቢ ድርሻ የጥበቃ ክልሉን ወይም መስህቡን በሚያዋስኑት ቀበሌዎች ቁጥር ብዛት የሚወሰን ይሆናል::

10.3. የገቢ አጠቃቀሙ ሥርዓት በቀጥታም ሆነበተዘዋዋሪ የመስህቡን ጥበቃና ልማት ለማይጻረር ተግባር መዋልይኖርበታል፡፡

10.4. የአጠቃቀም ሥርዓቱየክልሉ”መንግስትየፋይናንስህግናደንብየተከተለመሆንአለበት፡፡

**10.5**የአደን ቦታ መጠቀሚያ ግብር የአደን ክልሉ ላለበት ወረዳ/ዎች/ በቀጥታ የሚከፈል እና በገቢ ክፍፍሉ የማይካተት ይሆናል።

11.<u>ክትትልናቁጥጥር ስለማድረግ</u>

የክልሉየባህልና ቱሪዝም ቢሮ ንዲሁም በተዋረድ ያሉየዞንና የልዩ ወረዳ እና ወረዳዎች ባህል፣ ቱሪዝምና መንግሥት ኮሚንኬሽን ጉዳይ መምሪያ ፅ/ቤት ወይም እነዚህን መስሪያ ቤቶች የሚወኩሏቸው መ/ቤቶች የክትትልና የቁጥጥሩን ሥራ ያከናውናል።

# **<u>ክፍል አምስት</u>**

# **<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>**

12. ***<u>መመሪያስለማውጣት</u>***

ቢሮው ደንቡን ለማስፈጸም የሚረዱ ዝርዝር መመሪያችን እንደአስፈላጊነቱ ሊያወጣ ይችላል፡፡

13.***<u>ተፈጻሚነት የሌላቸው ህጎች</u>***

1. ደንብ ቁጥር 65/2000 በዚህ በደንብ ተሸራል፡፡
2. ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ደንቦች፣ መመሪያዎችና ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

***14.<u> ደንቡ ስለሚሻሻልበት ሁኔ</u>***

እንደአስፈላጊነቱ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን ደንብ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

15.***<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>***

*ይህ ደንብበክልሉ መንግስት ከጸደቀበት ከ ________ ቀን* ***2005*** *ዓ.ም ጀምሮ የጸናይሆናል፡፡*

**ሽፈራው ሽጉጤ**
የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር
*<u>ሀ ዋሳ</u>*

## አዝል

## <u>የአገልግሎት አይነቶችና የክፍያ መጠን</u>የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ተ/ቁ | የአገልግሎት አይነት | የክፍያ መጠን | |
|---|---|---|---|
| | | ብር | ሣ |
| | ሀ. የመግቢያ ክፍያ | | |
| 1 | የብሄራዊ ፓርክ ጉብኝት (ለ24 ሰዓት) | | |
| 1.1 | የውጭ አገር ዜጋ | አ.በዶላር 10 | 00 |
| 1.2 | ኢትዮጵያዊ | 20 | 00 |
| 1.3 | ለሃገርህን ዕወቅ ክበባት አባላት | 10 | 00 |
| 1.4 | ተማሪዎች | 5 | 00 |
| 1.5 | በት/ቤት ለተቋቋሙ ክበባት አባላት | 3 | 00 |
| 2 | <u>ለአዞ ራንች ጉብኝት (ለ24 ሰዓት</u> | | |
| 2.1 | የውጭ አገር ዜጋ | አ.ዶላር 10 | 00 |
| 2.2 | ኢትዮጵያዊ | 20 | 00 |
| 2.3 | ለሃገርህን ዕወቅ ክበባት አባላት | 10 | 00 |
| 2.4 | ተማሪዎች | 5 | 00 |
| 2.5 | በት/ቤት ለተቋቋሙ ክበባት/ተማሪዎች | 3 | 00 |
| 3 | <u>ህብረተሰብለሚተዳደሩየቱሪስት መስህቦች ጉብኝት /ለ24 ሰዓት/</u> | | |
| 3.1 | የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች | | |
| 3.2 | የውጭሃገርዜጋ | አ.ዶላር 10 | 00 |
| 3.3 | ኢትዮጵያዊ | 10 | 00 |
| 3.4 | የሃገርህን ዕወቅ ክበባት አባላት | 5 | 00 |
| 3.5 | ተማሪዎች | 5 | 00 |
| 3.6 | በት/ቤት ለተቋቋሙ ክበባት | 3 | 00 |
| 4 | ለሌሎች ተፈጥሮአዊ፣ባህላዊና ታሪካዊ መስህቦች | | |
| 4.1 | የውጭሃገርዜጋ | አ.ዶላር 6 | 00 |
| 4.2 | ኢትዮጵያዊ | 10 | 00 |
| 4.3 | የሃገርህን ዕወቅ ክበባት አባላት | 5 | 00 |
| 4.4 | ተማሪዎች | 2 | 00 |
| 4.5 | በት/ቤት ለተቋቋሙ ክበባት | 2 | 00 |
| | ለ. ሌሎች አቅርቦቶችና አገልግሎቶች ክፍያ | | |
| 5 | ለአጃቢ እስካውት ክፍያ | | |
| 5.1 | ለውጪ ዜጋ | | |
| 5.1.1 | በአንድ ጉዞ ከ12 ሰዓት ላልበለጠ አገልግሎት | አ.ዶላር 6 | 00 |
| 5.1.2 | በአንድ ጉዞ ከ24 ሰዓት ላልበለጠ አገልግሎት | አ.ዶላር 10 | 00 |
| 5.2 | ለሀገር ውስጥ ጎብኚ | | |
| 5.2.1 | በአንድ ጉዞ ከ12 ሰዓት ላልበለጠ አገልግሎት | 70 | 00 |

| ተ/ቁ | የአገልግሎት አይነት | የክፍያ መጠን | |
|---|---|---|---|
| | | ብር | ሣ |
| 5.2.2 | በአንድ ጉዞ ከ24 ሰዓት ላልበለጠ አገልግሎት | *100* | 00 |
| 6 | **አውሮፕላን ማረፊያ አገልግሎት** | | |
| 6.1 | **ባለአንድ ሞተር** | | |
| 6.1.1 | ለአንድ ጊዜ አርፎ ለመነሳት ብቻ | 300 | 00 |
| 6.1.2 | ለ24 ሰዓት አርፎ ለመቆየት ብቻ | 200 | 00 |
| 6.2 | **ባለሁለት ሞተር** | | |
| 6.2.1 | ለአንድ ጊዜ አርፎ ለመነሳት ብቻ | 600 | 00 |
| 6.2.2 | ለ24 ሰዓት አርፎ ለመቆየት ብቻ | 300 | 00 |
| 7 | **የተሽከርካሪ ክፍያ /ለአንድ ጊዜ የአንድ ተሽከርካሪ** | | |
| **7.1** | **የመኪና ክፍያ** | | |
| 7.1.1 | የውጭሃገርዜጋ | | |
| 7.1.1.1 | ከአስራ ሁለት ሰው በላይ ለሚጭን | አ.ዶላር 4 | 00 |
| 7.1.1.2 | ከሰባት እስከ 12 ለሚጭን | አ.ዶላር 3 | 00 |
| 7.1.1.3 | ስድስት ሰውና በታችለሚጭን | አ.ዶላር 2 | 00 |
| 7.1.2 | ለኢትዩጵያዊ | | |
| 7.1.2.1 | ከአስራ ሁለት ሰው በላይ ለሚጭን | 60 | 00 |
| 7.1.2.2 | ከሰባት እስከ 12 ለሚጭን | 40 | 00 |
| 7.1.2.3 | ስድስት ሰውና በታችለሚጭን | 30 | 00 |
| **7.2** | **የሞተር ብስክሌት ክፍያ** | | |
| **7.2.1** | የውጭሃገር ዜጋ | አ.ዶላር 2 | 00 |
| **7.2.2** | ለኢትዮጵያዊ | 10 | 00 |
| **7.3** | **የጀልባ ክፍያ** | | |
| **7.3.1** | የውጭሃገር ዜጋ | አ.ዶላር 8 | 00 |
| **7.3.2** | ለኢትዮጵያዊ | 50 | 00 |
| 8 | **የጀልባ ክራይ ለአንድ ጉዞ ከሁለት ሰዓት ላልበለጠ ጊዜ** | | |
| 8.1 | የውጭ ሃገር ዜጋ | አ.ዶላር 30 | 00 |
| 8.2 | ለኢትዮጵያዊ | 300 | 00 |
| 9 | **በአስጎብኚ ድርጅቶች የሚከፈል ክፍያ /ለአንድ ጉዞ በተሽከርካሪ/** | | |
| 9.1 | ብሔራዊ አስጎብኚ ድርጅት | 80 | 00 |
| 9.2 | የክልሉ አስጎብኚ ድርጅት | 50 | 00 |
| 10 | **ለማረፊያ ስፍራ /በድንኳን መጠን ለአንድ ቀን/** | | |
| 10.1 | **ከአራትሰውበላይለሚይዝ** | | |
| 10.1.1 | የውጭሀገርዜጋ | አ.ዶላር4 | 00 |
| | ኢትዮጵያዊ | 30 | 00 |
| 10.2 | **አራት ሰውና በታች ለሚይዝ** | | |
| 10.2.1 | የውጭ ሀገር ዜጋ | አ.ዶላር3 | 00 |
| 10.2.2 | ኢትዮጵያዊ | 20 | 00 |

| ተ/ቁ | የአገልግሎት አይነት | የክፍያ መጠን | |
|---|---|---|---|
| | | ብር | ሣ |
| 11 | ለድንኳን ኪራይ /በድንኳን መጠን ለአንድ ቀን/ | | |
| 11.1 | የውጭሃገርዜጋ | | |
| 11.1.1 | አራትና ከዚያ በላይ ሰው ለሚይዝ | አ.ዶላር12 | 00 |
| 11.1.2 | ከአራት ሰው በታች ለሚይዝ | አ.ዶላር10 | 00 |
| 11.2 | ኢትዮጵያዊ | | |
| 11.2.1 | ከአራት ሰው በላይ ለሚይዝ | 100 | 00 |
| 11.2.2 | ከአራት ሰው በታች ለሚይዝ | 60 | 00 |
| 12 | ለንግድ ሥራ ለሚደረግ ቀረጻ /በአንድ ጊዜ ለአንድ ቦታ ብቻ/ | | |
| 12.1 | የፊልም ቀረጻ / ተፈጥሮዊና ታሪካዊ ቅርሶች/ | | |
| 12.1.1 | በመኪና | | |
| 12.1.1.1 | ኢትዮጵያዊ/ድርጅት | 5000 | 00 |
| 12.1.1.2 | የውጭ ሃገር ዜጋ/ድርጅት | አ.ዶ 3000 | 00 |
| 12.1.2 | በአውሮፕላን | | |
| | ኢትዮጵያዊ/ድርጅት | 8000 | 00 |
| | የውጭ ሃገር ዜጋ/ድርጅት | አ.ዶላር 5000 | 00 |
| 12.1.3 | በተሽከርካሪና በአውሮፕላን | | |
| 12.1.3.1 | ኢትዮጵያዊ/ድርጅት | 13000 | 00 |
| | የውጭ ሃገር ዜጋ/ድርጅት | አ.ዶላር 8000 | 00 |
| 12.1.2 | ባህላዊ ሀብቶች | | |
| 12.1.2.1 | በመኪና | | |
| | ኢትዮጵያዊ/ድርጅት | 6000 | 00 |
| | የውጭ ሃገር ዜጋ/ድርጅት | አ.ዶላር 4500 | 00 |
| 12.1.2.2 | በአውሮፕላን | | |
| | ኢትዮጵያዊ/ድርጅት | 10000 | 00 |
| | የውጭ ሃገር ዜጋ/ድርጅት | አ.ዶላር 7500 | 00 |
| 12.1.2.3 | በተሽከርካሪና በአውሮፕላን | | |
| | ኢትዮጵያዊ/ድርጅት | 16000 | 00 |
| | የውጭ ሃገር ዜጋ/ድርጅት | አ.ዶላር12000 | 00 |
| 12.2 | የፎቶ ግራፍ ቀረጻ | | |
| | ኢትዮጵያዊ/ድርጅት | 200 | 00 |
| | የውጭ ሃገር ዜጋ/ድርጅት | አ.ዶላር 12 | 00 |
| 13 | ክልላዊ ልዩ ልዩ የዱር እንስሳት አጠቃቀም ክፍያ | | |
| 13.1 | የሀገር ውስጥ ነዋሪ አደን ፈቃድ ማውጫ | 2000 | 00 |
| 13.2 | የዱር እንስሳት ጠመዳ ባለሙያ ፈቃድ | 1000 | 00 |
| 13.3 | የውጪ ተመራማሪዎች ሳይንሳዊ ጥናት | አ.ዶላር 1000 | 00 |
| 13.4 | የዱር እንስሳት ውጤቶች ንግድ ፈቃድ | 2500 | 00 |

| ተ/ቁ | የአገልግሎት አይነት | የክፍያ መጠን | |
|---|---|---|---|
| | | ብር | ሣ |
| 13.5 | የታክሲ ደርሚ ስራ ፈቃድ | 2000 | 00 |
| 13.6 | **የዱር እንስሳት እርባታ ፈቃድ** | | |
| 13.6.1 | ሰጎን | 400 | 00 |
| 13.6.2 | አዞ | 400 | 00 |
| 13.6.3 | ጥርኝ | 200 | 00 |
| 13.7 | **የአዞ፣ የጥርኝ፣ የሰጎን ነፍስ ወከፍ ዋጋ ተመን** | | |
| 13.7.1 | **ጥርኝ (ወንድ)** | | |
| | ለውጪ ዜጋ ኢንቨስተር | ኢ.ዶላር 15 | 00 |
| | ለኢትዮጲያዊ ኢንቨስተር | 20 | 00 |
| | ለአርሶ አደር /አርብቶአደር | | |
| | 1. ከ11-50 ጥርኝየሚያረባ ከሆነ | 2 | 00 |
| | 2. ከ51-100ጥርኝ የሚያረባ ከሆነ | 5 | 00 |
| 13.7.2 | **የአዞ ጫጩት** | | |
| | ለውጪ ዜጋ ኢነቨስተር<br>ለኢትዮድያዊ ኢንቨስተር<br>ለአርሶ/አርብቶ አደር ከሆነናከ100 በላይ ጫጩት ከሆነ | ኢ.ዶላር 15<br>50<br>30 | 00<br>00<br>00 |
| 13.7.3 | **የአዞ እንቁላል መሸጫ ዋጋ** | ኢ.ዶላር 5 | 00 |
| 13.7.4 | **የሰጎን ጫጩት** | | |
| | 1 ለውጪ ዜጋ ኢንቨስተር<br>2 ለኢትዮጽያዊ ኢነቨስተር<br>3 ለአርሶ/አርብቶ አደር<br>ከ100በላይ ከሆነ<br>ከ100በታች ከሆነ | ኢ.ዶላር 15<br>50<br>10<br>15 | 00<br>00<br>00<br>00 |
| 13.7.5 | ***የሰጎን እንቁላል*** | | |
| | *1 ለውጪ ዜጋ ኢንቨስተር*<br>*2 ለኢትዮÉያዊ ኢነቨስተር*<br>*3 ለአርሶ/አርብቶ አደር*<br>*ከ100 በላይከሆነ*<br>*ከ100 በታች ከሆነ* | ኢ.ዶላር 10<br>30<br>15<br>20 | 00<br>00<br>00<br>00 |
| 13.8 | **ስፖርታዊ አሳ ማጥመድ /በዝርያና በንፍስ ወከፍ/** | | |
| 13.8.1 | **ነጭ ዓሳ** | | |
| | 1 ለውጪ ዜጋ ጎብኚ /<br>2 ለኢትዮጵያዊ ጎብኚ | ኢ.ዶላር 20<br>200 | 00<br>00 |
| 13.8.2 | **ቆሮሶ** | | |
| | 1 ለውጭ ዜጋ ጎብኚ | ኢ.ዶላር 15 | 00 |
| | 2. ለኢትዩÉያዊ ጎብኚ ብር | | |
| 13.8.3 | **አምባዛ** | | |

| ተ/ቁ | የአገልግሎት አይነት | የክፍያ መጠን | |
|---|---|---|---|
| | | ብር | ሣ |
| | 1 ለውጪ ዜጋ ኅብ'ኒ ብር<br>2 ለኢትዮጵያዊ ኅብ'ኒብር | አ.ዶላር 10<br>50 | 00<br>00 |
| **13.8.4** | **ሌሎች የዓሳ ዝርያዎች** | | |
| 14. | **ዓመታዊ የአደን ቦታ /ኮንሶሽን/ ክፍያ** | 100000 | 00 |